

# እስጢፋኖስ የመጀመሪያው ክርስቲያን አርበኛ

❊ እስጢፋኖስ በመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ከነበሩት ታላላቅ የእምነት ሰዎች አንደኛው ነበር። ሐዋርያ ባይሆንም በኢየሩሳሌም የነበሩ መበለቶችን እንዲያገለግል (እንዲንከባከብ) የተመረጠና በአዲስ ኪዳን ውስጥ ለየት ያለ ቦታ የነበረው ሰው ነው። አንዳንዶቹ መበለቶች ቸል ተብለው እንደነበር እናስታውሳለን። ስለዚህ እስጢፋኖስና ሌሎች ስድስት "በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ የእምነት ሰዎች" ሰዎች እነኝህን መበለቶች እንዲያገለግሏቸው ተመረጡ።

❊ እስጢፋኖስ በተጨማሪም የመጀመሪያው አርበኛ ነበር። አርበኛ ማለት እስከ ሞት ድረስ እምነቱን አጥብቆ የሚይዝ ሰው ማለት ነው። እስጢፋኖስም በጌታ ኢየሱስ ላይ የነበረው እምነቱ እንዲህ አይነት ነበር።

❊ ሌላው  እስጢፋኖስን ለየት የሚያደርገው ደግሞ ተአምራትን ማድረጉ ነበር። በአንድ ወቅትም መስበክ ጀመረ። እናም ከአይሁዳውያን አንዳንዶች በኢየሱስ ክርስቶስ ስለነበረው እምነት ከእርሱ ጋር መከራከር ጀመሩ። እነኝህ ክፉ ሰዎች እስጢፋኖስን በክርክር መርታት ስላልቻሉ በሙሴና በእግዚአብሔር ላይ ሐሰትን ይናገራል ብለው ሰዎችን ሁሉ አነሳሱበት። ይህ እውነት አልነበረም።  ሆኖም ብዙ ሰዎች እነኝህ ክፉ ሰዎች ያሏቸው ትክክል እንደሆነ ስላመኑ እጅግ በጣም ተበሳጩ።

❊ ከዚያም እስጢፋኖስን  ወደአይሁድ መሪዎች ሸንጎ ይዘውት መጡ። እነዚህ የአይሁድ መሪዎች በአንድ ሰው ላይ እስከ ሞት የሚደርስ ውሳኔ የመወሰን ስልጣን ያላቸው ነበሩ።
ነገር ግን እስጢፋኖስ እውነትን እንዳይናገር የሚከለክለው አንዳችም ፍርሃት በውስጡ አልነበረም። በፊታቸው እንደቆመም ፊቱ እንደመልአክ ፊት ሲለወጥ ተመለከቱ።

❈ ከአብርሃም ጀምሮ እስከኢየሱስ ክርስቶስ ድረስ ያለውን ታሪክ ተረከላቸው። ከዚያም አድማጮቹንና ከእነርሱ በፊት የነበሩትን አባቶቻቸውን ነቢያትን በመደብደብና በመግደል ኃጢአት ከሰሳቸው። ከዚያ አልፈውም ፃድቅ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን መግደላቸውንም ኮነነ። ይህን ያደመጡ መሪዎችም እጅግ በጣም ተቆጡ። እስጢፋኖስም ወደሰማይ ሲመለከት የእግዚአብሔርን ክብር አየ። እንደዚሁም ኢየሱስ ክርስቶስን በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየ። እያየ የነበረውን ራዕይም ለሰዎቹ ተናገረ።

❈ ይናገር የነበረውን ነገር መስማት ስላልፈለጉም እጆቻቸውን በጆሮዎቻቸው ላይ አድርገው ጮኹበት። እየጎተቱ ከከተማይቱ ካወጡት በኋላም በድንጋይ ደብድበው ገደሉት።

❈ በድንጋይ እየደበደቡት ሳለም እስጢፋኖስ፣ “ጌታ ኢየሱስ ሆይ! ነፍሴን ተቀበል። እንኼህንም ይቅር በላቸው፣” በማለት ፀለየ። ይህንንም ብሎ አንቀላፋ (ሞተ)።

❈ እስጢፋኖስ ልክ እንደኢየሱስ ክርስቶስ የምሕረት መንፈስ ነበረው። ታስታውሱ እንደሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሆኖ ተመሳሳይ ቃላትን ተናግሮ ነበር።

❈ የጠርሴሱ ሳውል የሚባለው አንድ ወጣትም በእስጢፋኖስ ሞት ተስማምቶ ነበር።

*የእስጢፋኖስን ታሪክ በሐዋርያት ስራ ምዕራፍ 6 እና ምዕራፍ 7 ውስጥ እናገኛለን።*

http://gardenofpraise.com